

የዕለተ ፡ ዓርብ ፡ የቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ካህን ፡ ገድል

፩ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብና ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ በዓርብ ፡ ቀን ፡ የሚነበብ ፡ የቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ገድል ፡ ምሥክርነት ፡ የቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ካህን ፡ በረከት ፡ ከአገልጋዮቹ ፡ ከ ና ፡ ከ ጋር ፡ ይኑር ፡ ለዘለዓለሙ ፡ አሜን።

፪ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ያመሰግናል ፡ ሁላቸው ፡ የአምሳያው ፡ ልጆቹም ፡ አቅማቸው ፡ በሚችለው ፡ በታላቅ ፡ ድምጽ ፡ ያመሰግናሉ ፡ ኢሳይያስ ፡ እንዳየ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሱራፌል ፡ ሲያመሰግኑት።

፫ ፡ እንደገናም ፡ በመጽሐፈ ፡ ሕፁፃን ፡ ስለመዘምራን ፡ በጸናጽልና ፡ በማሲንቆ ፡ በከበሮና ፡ በመለከት ፡ ድምጽ ፡ እንዲያመሰግኑ ፡ በፍሥሐና ፡ በደስታ ፡ ቃልም ፡ ወደ ፡ አርያም ፡ ቃሎቻቸውን ፡ ከፍ ፡ እንዲያደርጉ ፡ ሌዋውያንን ፡ አቆማቸው ፡ እግዚአብሔርንም ፡ አመሰግኑት ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ከዓለም ፡ በፊት ፡ እስከዚህ ፡ ለዓለም ፡ ሁሉ ፡ ሕዝብ ፡ ይሁን ፡ ይሁን ፡ ይበሉ።

፬ ፡ ያሬድ ፡ ካህንም ፡ በሚያመሰግንበት ፡ ጊዜ ፡ በታላቅ ፡ ቃል ፡ ይጮኻል ፡ ያመሰግናልም ፡ ቃሉም ፡ በምድር ፡ ሳለ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ይደርሳል ፡ የገድሉ ፡ መጽሐፍ ፡ እንዳለም ፡ የነቢይ ፡ ዕዝራ ፡ መጽሐፍም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ መታደስ ፡ ጊዜ ፡ ካህናትን ፡ በየአውራጃዎቻቸው ፡ ፈለጓቸው ፡ በደስታና ፡ በሞዐውዑት ፡ በጸናጽልና ፡ በምስጋና ፡

በማኅሌትም ፡ ምስጋና ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ

፭ መዘምራንም ፡ ከሁሉ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ አገር ፡ አውራጃዎች ፡ ከክፍለ ፡ አገሮች ፡ ከሁሉ ፡ ቦታዎች ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚያመሰግኑ ፡ ተሰበሰቡ ፡ ሁላቸው ፡ እስራኤል ፡ በአንድነት ፡ አመሰገኑ ፡ መዘምራንም ፡ ደጃፍ ፡ ዘጊዎችም ፡ ሁሉ ፡ ጊዜ ፡ ምስጋናን ፡ ይተጋገዙ ፡ እኔ ፡ በፈቴሽት ፡ እንዳመሰግን ፡ አወቁ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሕንፃ ፡ መታደስ ፡ በደስታና ፡ በሞዐውዑት ፡ በማኅሌትና ፡ በምስጋና ፡ ምስጋናን ፡ ያደርጉ ፡ ካህናትን ፡ አምጡዋቸው ፡ ይላልና።

፮ ፡ ያሬድ ፡ ካህንም ፡ ያመሰግናል ፡ ይዘምራልም ፡ ይቀኛልም ፡ በፈቴሽትና ፡ በታላቅ ፡ ድምጽ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወንጌላውያን ፡ የሆኑ ፡ የትምህርቱ ፡ ልጆችም ፡ ለአምላካቸው ፡ ለግእዚአብሔር ፡ ስም ፡ ያመሰግናሉ።

፯ ፡ በነቢዩ ፡ ሲራክ ፡ መጽሐፍም ፡ ዳዊት ፡ መዘምራኖቹን ፡ እንደሾመና ፡ በሁሉ ፡ ክብሩ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑት ፡ እንዳለ ፡ ተነገረ ፡ ተባለ ፡ ተባለም ፡ ፈጣሪውን ፡ ወደደው ፡ የመሠውያው ፡ መዘምራንም ፡ አቆመ ፡ የድምጻቸው ፡ ፈቴሽትም ፡ ጣፋጭና ፡ የሚያምር ፡ ነው ፡ ያሬድ ፡ ካህንም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መዘምርን ፡ ሆነ ፡ በወንጌል ፡ ካመኑ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ በፈቴሽትና ፡ በታላቅ ፡ ድምጽ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግናል ፡ የድምጻቸው ፡ ፈቴሽትም ፡ ጣፋጭና ፡ የሚያምር ፡ ነው።

፮ ፡ ነቢይ ፡ ኢሳይያስ ፡ አለ ፡ በኃይለሀ ፡ ታላቅ ፡ ምስጋናን ፡ ለጽዮን ፡ የሚነግርላት ፡ ወደ ፡ ረጅም ፡ ተራራ ፡ ይውጣ ፡ አለ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ የምትነግራት ፡ ቃልህን ፡ እንሣ ፡ አመስግን ፡ አትፍራ ፡ ለይሁዳ ፡ ክፍለ ፡ አገሮችም ፡ እነሆ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችሁ ፡ ከሰልጣኑ ፡ ጋር ፡ ይመጣል ፡ በኋቸው ፡ በሥልጣኑም ፡ ይፈርዳል ፡ እነሆ ፡ ዋጋው ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ ሥራውም ፡ በፊቱ ፡ ነው ፡ በጎቹን ፡ ይሰበስባል ፡ ያሬድ ፡ ካህንም ፡ ወደረኛም ፡ ተራራ ፡ ወጣ ፡ እሷም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ናት።

፯ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ በታላቅ ፡ ድምጽና ፡ ጩኸት ፡ ነገራት ፡ ለልጆቹም ፡ የክርስቶስ ፡ ምሥጢራትን ፡ ነገራቸው ፡ በታላቅ ፡ ጩኸት ፡ ሰማያትና ፡ ምድር ፡ ማይችሉት ፡ መምጣቱና ፡ ከድንግል ፡ ማኅፀን ፡ ማደሩ ፡ ማስተማሩም ፡ ነገራት ፡ ድንግልም ፡ የድንግልዋን ፡ ማኅተም ፡ ሳይጠፋ ፡ እንደጸነሰችው ፡ የአማኑኤል ፡ ክቅድስት ፡ ድንግል ፡ የሥጋ ፡ ቍልፍ ፡ ሳይከፍት ፡ መወለዱንም ፡ ነገራት።

፰ ፡ የሥጋዋ ፡ ድንግልና ፡ ኅቱም ፡ ሲሆን ፡ ለእርግዝናም ፡ እንደገባ ፡ የድንግልናዋ ፡ ማኅተም ፡ ሳይፈታ ፡ እንደተወለደም ፡ ዳግመኛም ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መገረዝንም ፡ ነገራት ፡ በዮርዳኖስ ፡ ወንዝ ፡ በዮሐንስ ፡ እጅ ፡ መጠመቁም ፡ እንደገና ፡ ሕማማቱን ፡ ሞቱን ፡ ትንሣኤውና ፡ ወደ ፡ ሰማያት ፡ ማረጉን ፡ በአባቱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቀኝ ፡ መቀመጡን ፡ ነገራት።

፲፩ ፡ ዳግመኛም ፡ ከአባቱና ፡ ከቅዱስ ፡ መንፈሱ ፡ ጋር ፡ ሕያዋንና ፡ ሙታንን ፡ እንዲፈርድ ፡ ይህንን ፡ ሁሉ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነገራት ፡ በታላቅ ፡ ጩኸት ፡ እያመሰገነ ፡ ሁላቸው ፡ የትምህርቱ ፡ ልጆችም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይህንን ፡ ማኅሌትን ፡ ያመሰግናሉ ፡ ይፈጭሻሉ ፡ ሌላ ፡ የሚልቅ ፡ የዓለም ፡ ነገርም ፡ አይደለም ፡ ነቢያት ፡ የጻፉት ፡ ትንቢታቸውን ፡ ሐዋርያት ፡ የጻፉት ፡ ትምህርታቸው ፡ ሁሉ ፡ ሥርዓታቸው ፡ እንደጻፉት ፡ እነሆ ፡ በሱ ፡ አለ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከሐዲዎች ፡ እነ ፡ ሐናንያ ፡ እነ ፡ ሴዴቅያ ፡ ተነሡ ፡ በነቢያት ፡ ትንቢትም ፡ ጨመሩ ፡ ሲሞንም ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ከሐዲዎች ፡ ዋሉ ፡ በሐዋርያት ፡ ሃይማኖትም ፡ ጨመሩ ፡ የያሬድ ፡ ካህን ፡ የማኅሌቱ ፡ ዜማም ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ አለ ፡ እስከ ፡ ጎልቀተ ፡ ዓለምም ፡ ይኖራል ፡ ፀሐይና ፡ ጨረቃ ፡ ከዋክብትም ፡ በሥርዓታቸው ፡ ዓለም ፡ ብቻቸው ፡ ሲያበሯት ፡ ያለ ፡ እሳቸው ፡ በስተቀር ፡ እስከ ፡ በሰማይ ፡ በታች ፡ የሚያበራ ፡ ሌላ ፡ ብርሃን ፡ እንደሌለ።

፲፪ ፡ እንዲሁም ፡ የያሬድ ፡ ካህን ፡ የማኅሌቱ ፡ ዜማ ፡ አንዱ ፡ ግዕዝ ፡ ሁለተኛው ፡ ዜማ ፡ ዓራራይ ፡ ሦስተኛ ፡ ዜማ ፡ ዕዝል ፡ ከነዚህ ፡ በስተቀር ፡ ለሰው ፡ ሌላ ፡ ዜማ ፡ የለም ፡ ለወፎች ፡ ለአራዊት ፡ ለእንስሳ ፡ ጩኸት ፡ ከዚህ ፡ ይሆናል ፡ ከነቢያት ፡ ከሐዋርያት ፡ በኋላ ፡ በፊቱ ፡ የለም ፡ በኋላውም ፡ እንደያሬድ ፡ ካህን ፡ የሚዘምር ፡ የለም ፡ የቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ካህን ፡ በረከቱ ፡ ከባራቹ ፡ ከ

ና ፡ ከ

ጋር ፡ ይኑር ፡ ለዘለዓለሙ ፡ አሜን።

ተአምር በል ማክሰኞ ላይ ገጽ ፻፱ አለ።

፡ የእግዚአብሔር ፡ ማኅሌት ፡ ከማኅበረ ፡ ቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ እንዳይታጐል ፡ (እንዳይቋረጥ) ፡ እንደ ፡
ለማዕታት ፡ ታኅሣ ፡ ስለ ፡ ማኅሌተ ፡ እግዚአብሔርም ፡
ለማዕትን ፡ ሆነ ፡ የቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ካህን ፡ በረከት ፡
ከባሮቹ ፡ ከ ና ፡ ከ

ይህ

ፌ ፡ የበ ማት ፡ የሆነና ፡
በትዕግሥ ንጉሡ ፡ ዘንግንም ፡
ደሙን ፡ ፡ የቅዱስ ፡ ያሬድ ፡
ካህን ፡ ተ ባሮቹ ፡ ከ
ጋር ፡ ይኑር ፡
ለዘለዓለሙ ፡ አሜን።

ፍ ፡ እንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ መነኮሴ ፡ እኔ ፡ ሂድኩ ፡ አለ ፡
ከእንድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ ሰውም ፡ ወደ ፡
ኢየሩሳሌም ፡ ወረድኩ ፡ እሱም ፡ ያለ ፡ ጫማ ፡ ይሄዳል ፡
ጌታችን ፡ ወደ ፡ ተወለደውና ፡ ወደ ፡ ተሰቀለው ፡ ወደ ፡
ተቀበረውም ፡ ደርሰን ፡ ወደ ፡ ተጠመቀበት ፡ ዮርዳኖስ ፡
ከሂድንም ፡ በዚያም ፡ ተጠመቅን ፡ ከሱም ፡ ጠጣን ፡
የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔርን ፡
የሚፈራ ፡ መነኮሴም ፡ የሚጣፍጥ ፡ የዮርዳኖስ ፡ ውሀ ፡
አለ ፡ አለኝ ፡ ያሬድ ፡ ካህን ፡ ስለዚህ ፡ የተገዛለት ፡ ጣፋጭ
፡ ውሀ ፡ በተከዚ ፡ ዳርቻ ፡ በተከዚ ፡ ባሕር ፡ ማኸል ፡
በደረቅ ፡ የጠላ ፡ ስካር ፡ እንደ ፡ ተወውና ፡ እንደ ፡ ኃይለኛ
፡ በእግር ፡ አሳልፋቸዋለሁ ፡ የባሕር ፡ ድምጽም ፡ እንደ ፡
አንበሳ ፡ ድምጽ ፡ ነው።

፫ ፡ ከሱም ፡ ይሀንን ፡ በሰማሁ ፡ ጊዜ ፡ ላየውም ፡ ልቤ ፡ ተጋ ፡ ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ወደ ፡ አገሬ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተመለስሁ ፡ ለዚያ ፡ መነኮሴም ፡ ከዚያ ፡ ተውሁት ፡ ወደ ፡ ተከዚም ፡ ደረስሁ ፡ ውሀ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ድምጽ ፡ የሚደምጽባት ፡ (የሚሰማባት) ፡ ቦታ ፡ አገኛት ፡ ዘንድም ፡ ተመላለስሁ ፡ እንዳመለከተኝም ፡ አገኘኋት ፡ ከዚያው ፡ ውሀም ፡ ጠጣሁ ፡ እንደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ውሀም ፡ ጣፊጠኝ።

፬ ፡ እንደገና ፡ በሱ ፡ ተጠመቅሁ ፡ ከዚህም ፡ በትጋትና ፡ በንቃት ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ በረሀ ፡ ዞርሁ ፡ የቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ካህን ፡ መቃብርን ፡ አገኝ ፡ ዘንድ ፡ አላገኘኘሁትም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሁለት ፡ መነኲሰትን ፡ አገኘኋቸው ፡ የያሬድ ፡ ካህን ፡ መቃብርንም ፡ እንደ ፡ አገኙትም ፡ ነገሩኝ ፡ ከሳቸው ፡ አንዱም ፡ በጌታችን ፡ ዕርገት ፡ ቀን ፡ በጸምኩ ፡ ጊዜ ፡ የያሬድ ፡ ካህን ፡ መቃብር ፡ አገኘሁት ፡ አለኝ ፡ ወደ ፡ መቃብሩ ፡ ደጃፍም ፡ ደረስኩ ፡ በዚያም ፡ ገባሁ ፡ ብዙ ፡ ተአምራትንም ፡ አየሁ ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የዕርገቱ ፡ ቀን ፡ የሆነች ፡ በአርባ ፡ ቀን ፡ የአርያም ፡ ቅኔ ፡ እያመሰገኑ ፡ ሰማሁ።

፭ ፡ ሁለተኛ ፡ አለኝ ፡ በተከዚ ፡ ዳርቻ ፡ አይደለም ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ጩኸት ፡ ውሀ ፡ የሚሰማበት ፡ ደረስኩ ፡ ያሬድ ፡ ካህን ፡ የባሕር ፡ ድምጽ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ እንደሆነ ፡ ሲል ፡ ሰለፀ ፡ የተገዛላት ፡ በዚያም ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ ጸምኩ ፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ሊላ ፡ ገዳም ፡ ሄድኩ ፡ ወደረጅም ፡ ተራራ ወጣሁ ፡

ያለ ፡ እሁዶች ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ በዚያ ፡ ጸምኩ ፡ ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ሕሊናየ ፡ ታወከች ፡ የሁለት ፡ ቀኖች መሄጃ ፡ ተነሥቼ ፡ ሄድኩ ፡ በማታ ፡ ጊዜ ፡ ደረስኩ ፡ የያሬድ ፡ ካህን ፡ መቃብር ፡ ወደሚባል ፡ የሚያስፈራ ፡ የመብረቅ ፡ ድምጽና ፡ የነጐድጓድ ፡ ታል ፡ ሆነ ፡ ያን ጊዜም ፡ ደነገጥኩ ፡ በፊቴም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ወደቅኹ ፡ አንቀጸ ፡ ብርሃንም ፡ እናገር ፡ ጀመርሁ ፡ ሳነብም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ወደእኔ ፡ በመነኮስ ፡ አምሳል ፡ መጣ ፡ ምን ትፈልጋለህ ፡ ወደዚህ ፡ የመጣህ ፡ ምንን ፡ ትወዳለህ ፡ አለኝ።

፮ ፡ እኔም ፡ የያሬድ ፡ ካህን ፡ በረከቱ ፡ ፈልጌ ፡ መጣሁ ፡ አልኩት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ያዘኝ ፡ እንደ ፡ ደጃፍ ፡ ወደ ፡ ማትታወቅ ፡ ደጃፍም ፡ ወሰደኝ ፡ ወደ ፡ ውስጧም ፡ አገባኝ ፡ እጅግ ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ የምታበራ ፡ ታላቅ ፡ አገርን ፡ አየሁ ፡ ያ ፡ ሰውየም ፡ ከዚያች ፡ የበራች ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ተኛ ፡ ሰው ፡ ያለበት ፡ አደረሰኝ ፡ ልብሱም ፡ ትልቅና ፡ እጅግ ፡ ነጭ ፡ ነው ፡ በራሱ ፡ አጠገብም ፡ ትልቅ ፡ መጽሐፍ ፡ ተቀምጧል ፡ የሚደገፈው ፡ በትርም ፡ በአጠገቡ ፡ አለ ፡ የሚመራኝ ፡ ሰውም ፡ ያሬድ ፡ ካህን ፡ ያ ፡ ነው ፡ አለኝ ፡ የተመረጠና ፡ የከበረ ፡ ቆብን ፡ ያደረገ ፡ መነኩሴና ፡ ሰማዕት ፡ ሰው ፡ መጽሐፍም ፡ ሲያመሰግንባት ፡ የነበረ ፡ ማኅሌቱ ፡ የሆነች ፡ መዝሙር ፡ ናት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ካህናትም ፡ የሚያስተምራቸው ፡ የሚደገፈው ፡ ብትርም ፡ እንደ ፡ በትረ ፡ ሙሴ ፡ የመሰለ ፡ ነው።

፮ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ የነበረ ፡ ሰውም ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ትንሽ ፡ ወሰደኝ ፡ ዘጠኝ ፡ የጻድቃን ፡ አብድንት ፡ ወደ ፡ አሉበትም ፡ ወሰደኝ ፡ ልብሳቸውም ፡ እጅግ ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ ነጭ ፡ ነው ፡ እንደግናም ፡ ከትልቅ ፡ መንበር ፡ ላይ ፡ ወዳለ ፡ ታቦት ፡ ወሰደኝ ፡ መስቀልም ፡ በዚያ ፡ አለ ፡ በስተቀኝም ፡ ትልቅ ፡ ባሕርን ፡ አየሁ ፡ ወደላይም ፡ አንጋጠጥሁ ፡ እንደ ፡ ነጐድጓድ ፡ ወደታች ፡ የሚንጠበጠብ ፡ ነጭ ፡ ውሀንም ፡ አየሁ ፡ ያ ፡ የሚንጠበጠብ ፡ ውሀም ፡ በውስጡ ፡ ይሰበስባል ።

፯ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ያለ ፡ ሰውም ፡ ከዚህ ፡ ውሀ ፡ ጠጣ ፡ አለኝ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ውሀ ፡ ጠጣሁ ፡ በልቤ ፡ ውስጥም ፡ ፍሥሐና ፡ ደስታ ፡ ሞላ ፡ በእኔ ፡ ላይም ፡ ኃይል ፡ አደረ ፡ የሥጋ ፡ ድካምም ፡ ከእኔ ፡ ተወገደ ፡ ጠናሁም ።

፰ ፡ ከዚህ ፡ በኋላም ፡ እጄን ፡ ይዞ ፡ ባገባኝ ፡ መስኩት ፡ አወጣኝ ፡ ከዋሻ ፡ ደጃፍ ፡ አቆመኝ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከእኔ ፡ ተሠወረ ፡ አጣሁትም ፡ ወደ ፡ ሄደውም ፡ አላወቅሁትም ፡ እኔንም ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ያደረ ፡ ኃይል ፡ ያዘኝ ፡ ፈጽሞ ፡ ወደ ፡ ቦታየ ፡ አደረሰኝ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥም ፡ ገባሁ ፡ ያየሁትና ፡ የሰማሁት ፡ የያሬድ ፡ ካህን ፡ ክብርንም ፡ እየተናገርኩ ፡ ተቀመጥሁ ፡ በቅዱሳን ፡ የሚመሰገን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገንኩት ፡ ለእኔም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ተገለጠልኝ ፡ ምስጋና ፡ ለተባረከው ፡ ሕያው ፡ አምላክ ፡ በአምላክ ፡ ምሕረት ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ አለሁ ።

፲ ፡ይህን ፡ ሁሉ ፡ አንድ ታማኝ ፡ የሆነ ሽማግሌና ፡ መነኮስ ፡ ሰውየ ፡ ነገረኝ ፡ በሚያስፈራ ፡ በታላቅ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ እየማለ ፡ የያሬድ ፡ ካህን ፡ በረከትና ፡ የማኅሌቱ ፡ ሀብት ፡ ከወዳጆቹ ፡ ከ

ና ፡ ከ ጋራ ፡ ይሁን ፡ ለዘለዓለሙ ፡ አሜን።